የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ የተዛማጅ ውሎች እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎች የፈቃድ አሰጣጥ፣ የአሰራር እና የቁጥጥር ረቂቅ መመሪያ ማብራሪያ

1. መግቢያ

ይህ የማብራሪያ ሃተታ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ፣ የተዛማጅ ውሎች እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የአሰራር እና የቁጥጥር ረቂቅ መመሪያ የሚመለከት ነው። ረቂቅ መመሪያው የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 ክፍል አራትን ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን ይህም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ የተዛማጅ ውሎች ገበያ እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ማቋቋሚያ አጠቃላይ መስፈርቶችን የሚያስቀምጥ ነው።

አዋጁ የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ እንደሚቋቋም የሚያመላክት ሲሆን የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መስፈርቱን አሟልቶ ሲገኝ የሰነደ ሙዐለ ንዋዮች ገበያ ፈቃድ እንደሚሰጠው የአዋጁ አንቀጽ 31(5) ይደነግጋል።

የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ የውጭ ኢንቨስተሮችን ጨምሮ በትብብር እንደሚቋቋም በአዋጁ አንቀጽ 31(1) ተደንግጓል። የግሉ ዘርፍ ፍላጎት ካላሳየ የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ሙሉ በሙሉ በመንግስት ባለቤትነት ስር የመንግስት ድርጅት ሆኖ እንዲቋቋም ይሄው አዋጅ በአንቀጽ 31(4) ያዛል። በተጨማሪም የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ለሌሎች የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች፣ ለተዛማጅ ውሎች ገበያዎች ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ላሉ የግብይት መድረኮች ፈቃድ መስጠት እንደሚችልም የአዋጁ አንቀጽ 32(1) ይፈቅዳል።

ባለስልጣኑ የሚያወጣው መመሪያ የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ እና ሌሎች የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያዎች ወይም የተዛማጅ ውሎች ገበያዎች ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ የግብይት መድረኮችን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ አነስተኛ የካፒታል መመዘኛ፣ የተገቢነት እና ብቁነት መመዘኛዎችን፣ የስራ እና ስራ አመራር ሁኔታን፣ የብቃት ማስረጃ እና ሌሎች ፈቃድ ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ መመዘኛዎችን መያዝ እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 31(5) እና 32(2) ተመላክቷል። በተጨማሪም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በአዋጁ አንቀጽ 32(3) መሰረት ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የሚገበያዩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እና ተዛማጅ ውሎችን በተመለከተ ተሳታፊዎችን፣ ውሎችን፣ ሁኔታዎችን እና መስፈርቶችን እንዲወስን ስልጣን ይሰጣዋል።

2. <u>የረቂቅ መመሪያው አስፈላጊነት እና የዝግጅት ሁኔታ</u>

የካፒታል ገበያ ለሃገራችን ኢኮኖሚ ቀጣይ እድገት ጉልህ ሚና የሚጫወት እንደመሆኑ የተማከለ እና ቁጥጥር የሚደረግበት የካፒታል ገበያ ማቋቋም አስፈላጊነት በካፒታል ገበያ አዋጁ ዝግጅት ወቅት በነበሩ መድረኮች በግልጽ ተንጸባርቋል። በየቦታው ተበታትኖ የሚገኘውን የካፒታል ገበያ ሰነዶች ግብይት ወደ አንድ ማዕከል በማምጣት ገበያው ለኢንቨስተሩ፣

ለመንግስት እና የግሉ ሴክተር ብሎም ለሃገር ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋፆ ማሳደግ እንደሚገባ ታምኖበታል፡፡ አብዛኞቹ ያደጉት ሃገራት የካፒታል ገበያ ሰነዶች የሚገበያዩበት ራሱን የቻለ ሕግ እና ግብይት የሚከናወንበት ገበያ (ተቋም) እንዲሁም ግብይቱን እና አጠቃላይ ሥነ-ምህዳሩን የሚቆጣጠር ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን አላቸው፡፡ ይህን ተከትሎ በካፒታል ገበያ አዋጅ አንቀጽ 31 እና 32 መሠረት የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ እና ሌሎች የግብይት መድረኮች አንዲቋቋሙ ይፈቅዳል፡፡ አዋጁ ይህን ይበል እንጂ ለገበያዎቹ ፈቃድ የሚሰጥበት እና ባለሥልጣኑ ቁጥጥር የሚያደርግበት አግብብ ዝርዝሩ በአዋጅ አልተቀመጠም ይልቁንም ለሚቋቋሙት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች፣ የተዛማጅ ውሎች ገበያዎች እና ለያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎች ፈቃድ የሚሰጥበት፣ ቁጥጥር የሚደረግበት እና አሰራሩን በተመለከተ ዝርዝሩ በባለሥልጣኑ መመሪያ እንደሚወጣ የተደነገገ በመሆኑ ይህንን መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የረቂቅ መመሪያው ዝግጅት የተጀመረው የመመሪያ አርቃቂ ቡድን በማደራጀት የተለያዩ ሃገራትን ተሞክሮ በመውሰድ እና ሕጎች ላይ ጥናት በማድረግ ነው፡፡ በረቂቅ መመሪያው ዝግጅት ጥናት ከተደረገባቸው የጋና፣ ናይጄሪያ፣ የፓኪስታን፣ የፕሊፒንስ፣ የአሜሪካ፣ የኬንያ እና ሌሎች የካፒታል ገበያ የሚገኝባቸው ሃገራት ተሞክሮ ተወስዷል፡፡ አርቃቂ ቡድኑ በተለያየ ጊዜ መመሪያው ተፈጻሚ ከሚሆንበት ዋንኛ ባለድርሻ አካል ከሆነው የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ጋር በጋራ ውይይት በማድረግ እና በጋራ በመስራት የተገኙ ግብአቶችን በመጠቀም ይዘቱና ቅርጹ ማስተካከያ ተደርጎባታል፡፡ በተጨማሪ መመሪያው ከሕዝቡ ጋር በተለያዩ ጊዜያት ውይይት የተደረገበት ሲሆን የአቀራረብ ግልጽነት ጥያቄዎች፣ በገበያው የሚኖረው የመንግስት ድርሻ፣ የግሉ ባለሃብት እና የውጭ ባለሃብቶች ድርሻ፣ አወቃቀሩ እና ሌሎች ተዛማጅ ጥያቄዎች ተነስቶ ማብራርያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ በፕሮጀክት ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በጋራ ምክክር በማድረግ የረቂቁ ይዘት ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን ተቀብለናል አካተናል፡፡ በተለይ የገበያው ፈቃድ ለመስጠት የሚፈለግ ዝቅተኛ የካፒታል መጠን፣ መመዘኛዎቹን፣ ስለሚኖረው የግብይት ሥርዓት እና ሌሎች ተነስተው ውይይት ተደርጎ ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል፡፡ ይህንን ሂደት ተከትሎ ረቂቅ ሰነዱ በካፒታል ገበያ ባለሥልጣን በበላይ አመራርና ቦርድ ሰፊና ጥልቅ ውይይት ተደርጎበት ጸድቋል፡፡

3. <u>የረቂቅ መመሪያው ይዘት</u>

ከርዕሰ ጉዳዩ ሰፊነት አንፃር እና ጉዳዩን ግልፅ ለማድረግ ሲባል ረቂቅ መመሪያው በአራት ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን አራተኛው የተለያዩ ድንጋጌዎችን ያካተተ ነው፡፡

ክፍል 1 (አንቀጽ1-10) በረቂቅ መመሪያው ውስጥ ለሁሉም ፈቃዶች ተፈጻሚ የሚሆኑ አጠቃላይ መስፈርት ድንጋጌዎችን ያስቀምጣል፡፡ ይሄ ክፍል የመመሪያውን ወሰን፣ ትርጉም የተሰጣቸውን ቃላት እና የማመልከቻውን ሂደት እንዲሁም የፈቃድ እድሳትን፣ የማመልከቻ ውድቅ መደረግን፣ እገዳን እና ስረዛን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ይይዛል፡፡

የረቂቅ መመሪያው ክፍል 2 (አንቀጽ 11-56) በአዋጁ መሰረት የተቋቋሙትን ሁለት አይነቶቹን የግብይት መድረኮች የሚመለከቱ ልዩ ልዩ መስፈርቶችን ይመለከታል፡፡ እነዚህ ሁለቱ ዓይነት

የግብይት መድረኮች አንደኛው ገበያን የተመለከተ ሲሆን ይህም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም የተዛማጅ ውሎች ገበያ ሲሆን በውስጡ የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የሚያጠቃልል ነው። ሁለተኛው ያልተማከለ በጠረጴዛ ዙሪያ ገበያን ሲያጠቃልል እሱም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ወይም በተዛማጅ ውል ለመገበያየት ሊሆን እንደሚችል በረቂቅ መመሪያው ክፍል 3 (አንቀጽ 57-69) እንዲካተት ተደርጓል።

ከአዋጁ አንቀጽ 2(48) እና 22(2) መረዳት እንደሚቻለው በእነዚህ ሁለት የግብይት መድረኮች መካከል ያለው ቀዳሚ ልዩነት ገበያ (Exchange) መደራጀት ያለበት ራሱን በራሱ እንደሚቆጣጠር ድርጅት (SRO) ሲሆን ይህ በሁለተኛው የግብይት መድረክ ማለትም ባልተማከለ በጠረጴዛ ዙሪያ ባለ የግብይት መድረክ ላይ አይሰራም።

4. <u>የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ልማት</u>

የረቂቅ መመሪያው ክፍል 1 በአዋጁ አንቀጽ 5 ላይ የተገለጸውን የባለስልጣኑ ዋና ዓላማዎች በግልጽ ያሳያል። በተለይም በአዋጁ አንቀጽ 6 መሠረት ፈቃድ የመስጠት ሥልጣኑንና ግዴታውን ከመወጣት ጋር በተገናኘ ባለስልጣኑ የገበያ ልማት ዓላማን አድርጎ መሆን እንዳለበት ለመረዳት ይቻላል። የገበያ ልማት አላማ መሰረት በማድረግ ባለስልጣኑ የሚሰጠውን የፈቃድ መጠን ለመገደብ እንደታሰበ ረቂቅ መመሪያው ላይ ተደንግጓል።

ለመገደብ ያስፈለገበትም ምክንያት በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ በሚቋቋመበት ገና በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት በርካታ የግብይት መድረኮች ወደ ስራ ከገቡ የገበያውን እድገትና ጥልቀት የሚያደናቅፉ ከመሆኑም በላይ በጅምር ገበያው ላይ የሚኖረውን የገንዘብ መጠን በተለያየ ቦታ ተከፋፍሎ እንዲቀመጥ ያደርጉታል። ከዚህም በላይ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያው በጅምር ላይ ከመሆኑ አንፃር አስፈላጊው ካፒታልና ሀብት፣ ዕውቀት፣ ክህሎት እንዲሁም ግንዛቤ ገና በመገንባት ሂደት ላይ መሆናችንም ልብ ሊባል ስለሚገባ ነው።

5. <u>ገበያው ራሱን በራሱ እንደሚቆጣጠር ድርጅት (SRO)</u>

የአዋጁ ከፍል ሶስት አንድ ተቋም ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ለመሆን የሚያስፈልገውን መመዘኛዎች ይዘረዝራል። በተጨማሪም ባለሥልጣኑ የአዋጁን ክፍል ሶስት መሰረት አድርጎ በሚያዘጋጀው መመሪያ ራሳቸውን በራሳቸው ለሚቆጣጠሩ ድርጅቶች ተጨማሪ ዝርዝር መመዘኛዎች ያወጣል።

ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት በካፒታል ገበያ ውስጥ የስነ-ምግባር ደንቦችን በማውጣት እና በማስፈፀም እንዲሁም በሌሎች ካፒታል ገበያዎች ውስጥ ያሉ ውጤታማ ልምዶች በመቅሰም የራሱን አባላት የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት። ይህም ራሱን በራሱ በሚቆጣጠረው ድርጅት እና በባለስልጣኑ መካከል ልዩ የሆነ የቁጥጥር ግንኙነትን ይፈጥራል።

ገበያው ራሱን በራሱ እንደሚቆጣጠር ድርጅት ተቆጣጣሪው አካል የቁጥጥር አላማዎቹን ማለትም የእንቨስተሮችን ጥበቃ፣ ፍትሃዊ ቀልጣፋና ግልጽ ገበያ በመፍጠር እና መዋቅራዊ የአደጋ ስጋቶችን በመቀነስ ረገድ በንቃት እንደሚያግዘው ይጠበቃል። ከዚህም ባሻገር ተቋሙ

እንደ አክሲዮን ማህበር ማለትም የግል ኢኮኖሚ ጥቅም እንዳለው አካል የሚመሰረት ቢሆንም፤ ገበያው ታማኝነትን ጨምሮ የሕዝብ ጥቅምን ያስቀድማል ተብሎ ይጠበቃል።

ገበያው ፍትሃዊ እና ስርዓት ያለው ግብይት እንዲኖር የእለት ተእለት ግብይትን መቆጣጠር ይጠበቅበታል። የገበያ እንቅስቃሴን በመከታተል ፈጣን ምላሽ በመስጠት የግብይት ስርዓቱን የሚያናጉ ወይም የተከለከሉ የግብይት ተግባራትን መገደብ ይጠበቅበታል።

የገበያ ቁጥጥር ተግባራት የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው። እነዚህም ቅኝት፣ግምገማ እና የገበያ እንቅስቃሴን ሪፖርት ማድረግ፣ የገበያ ተሳታፊ ኩባንያዎችን እና ሌሎች የተመዘገቡ ኩባንያዎችን ባህሪ ምርመራ፣ የገበያ ተሳታፊ ሥነ-ምግባር መቆጣጠር፣ የግብይት ማስቆሚያዎች መተግበር፣ እገዳዎችና ከምዝገባ መሰረዝ እና ለባለስልጣኑ እገዛ መስጠትን ያጠቃልላል። ይህም የሚተገበረው የገበያ ተሳታፊዎች የገበያው አባል ሲሆኑ፣ ወደግብይት ቅበላ እና በግብይት ለመቀጠል ይሚተገበሩትን ደንቦች ለማክበር ሲስማሙ ነው።

ስኬታማ የገበያ አሰራርን መተግበር የገበያ ታማኝነትን ለማረጋገጥ የተወሰዱ የቁጥጥር እና የክትትል እርምጃዎች፣ ታማኝነቱን ከማሳካት ጋር ተያይዞ ከሚወጣው ወጪ ጋር ሚዛን መጠበቅ ይጠይቃል። ከመጠን በላይ ቁጥጥርም ሆነ እና በቂ ያልሆነ ቁጥጥር ሁለቱም ጎጂ የመሆን አቅም አላቸው። ስለዚህ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ስነ-ምህዳር ገና በጅምር ላይ ያለ ከመሆኑ አንጻር ባለስልጣኑ የክትትል አካሄድ ከፍተኛ ትኩረት እና እይታን የሚጠይቅ ነው።

6. <u>ክፍል 2 የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም የተዛማጅ ውሎች ገበያ ፈቃድ (አንቀጽ 11-56)</u>

የረቂቅ መመሪያው ክፍል 2 የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን ጨምሮ እንደ ሰነድ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም እንደ ተዛማጅ ውሎች ገበያ ፈቃድ ለማግኘት ልዩ መስፈርቶችን ያስቀምጣል። ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ፈቃድ የሚጠይቅ አመልካች ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች መስፈርቶችን እንዲሁም በረቂቅ መመሪያው ክፍል 2 ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅበታል።

የገበያ ፈቃድ ለማግኘት አመልካቹ ተገቢውን የድርጅት ባለቤትነት እና ቁጥጥር፣ ብቃት እና ታማኝነት፣ የንግድ ዝግጅት እንዲሁም አስተዳደር ሊኖረው ይገባል። እንደዚህ ዓይነቱን ፈቃድ በተመለከተ ሊታወቁ የሚገባቸው ድንጋጌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ።

- ገበያው የሚተዳደረው በዳይሬክተሮች ቦርድ መሆን እንዳለበት፣ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሊኖረው እንደሚገባ፣ ሁለቱም በአዋጁ ላይ እንደተገለጸው የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣንን ይሁንታ እንደሚገባቸው በረቂቁ ተመልክቷል።

- ቦርዱ የገበያውን አስተዳደርና የውሳኔ አሰጣጥ አተገባበር የመወሰን እና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት መሆኑን፣ ይህም በድርጅቱ ውስጥ ያሉ ኃላፊነቶችን ማከፋፈል እና

የጥቅም ግጭቶችን በመከላከል የገበያውን ታማኝነት በሚያበረታታ መልኩ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

- መመሪያው የገበያው የባለቤትነት ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ፣ ይህም በገበያው ሥራ ላይ ጉልህ ተጽዕኖ በሚያደርጉ ሰዎች ማንነት ላይ ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ የሚያስገድድ ድንጋጌዎችን አካቷል። ባለስልጣኑ የገበያውን ውጤታማ ቁጥጥር፣ አሠራሩን ወይም መከበራቸውን እና የፈቃዱን መስፈርቶች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ምንም አይነት እክል አለመኖሩን ይገመግማል። ይህንንም ሲያደርግ በአስተዳደሩ እና በገበያው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ አካላትን ፍላጎት መጠን እና ማንነት ግምት ውስጥ በማስገባት መሆኑ እንደሚገባ በረቂቁ ተካቷል።

- ቴክኖሎጂ ከገበያ ፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶች ጋር ወሳኝ ቁርኝት አለው። ይህ ቁርኝትም የግብይት ሥርዓቱን ከብልሽት መጠበቅ፣ መቆራረጥ ወይም ስሕተቶች በሌለበት ሁኔታ ተግባራቶቹን ለመወጣት የሚያስችል በቂ አቅም ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣ ገበያው ሥርዓት ያልተከተል ግብይትን ለመከላከል የሚያስችል ተገቢ አሠራር እንዲኖር ማድረግ፣ ለምሳሌ የዋጋ ተለዋዋጭነትን/መዋዠቅን ለመቆጣጠር የሚረዱ ዘዴዎችን እና ቅድመ እና ድህረ ግብይት ቁጥጥርን እንደሚያካትት ይደነግጋል።

- ረቂቅ መመሪያው መረጃ አያያዝ እና ደህንነት አንጻር በዳታ ጥበቃ፣ በሳይበር አደጋዎች እና በገበያው ቀጣይነት ላይ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ያካተተ ሲሆን ገበያው ከቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶቹ ጋር በተያያዘ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ወይም ሌሎች የሚመለከታቸው የመንግስት ኤጀንሲዎች መስፈርቶችን የሚያሟሉ ማስረጃዎችን ማቅረብን እንዳለበት ይደነግጋል።

- ገበያው በተለያየ ሁኔታ በቂ ሀብቶች እንዲኖሩት ያስፈልጋል። ይህም አስፈላጊው ክህሎት እና የቴክኒክ እውቀት ያላቸው እንዲሁም አሰራሩን ለመምራት የሚያስችል በቂ እውቀት ያላቸው ሰራተኞች በብዛት መያዝን ያጠቃልላል። አንዳንድ ተግባራትን እና ስራዎችን ከድርጅት ውጭ በሶስተኛ ወገን ማሰራት ቢቻልም (outsource) መመሪያው የተወሰኑ ተግባራትን እንደ የግብይት ቅኝት፣ የግብይት ሥርዓቱን መቆጣጠር፣ ግብይት የማስቆም ወይም የማገድ ውሳኔዎችን በተመለከተ የተወሰኑ ተግባራትን በሶስተኛ ወገን ማሰራት እንደማይቻል በረቂቁ ተመላክቷል።

- ገበያው ከቁጥጥር ወይም ከክትትል ተግባራት ጋር ካሉት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ውስጠ-ደንቦችን ማውጣት ይጠበቅበታል። ይህም በገበያው አባልነትን፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ እና ቅበላ፣ የግብይት ደንቦችን፣ የዲሲፕሊን እርምጃ እና ማዕቀብ የመጣል ስልጣኑን የሚመለከቱ ውስጠ-ደንቦችን የሚያካትት ይሆናል። ራስን በራስ

እንደሚያስተዳድር ድርጅት ማንኛውም የእነዚህ ውስጠ-ደንቦች ማሻሻያ፤ በባለስልጣኑ ማስጸደቅ ይጠበቅበታል።

- የገበያው አባላት ፈቃድ ያላቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎችን ያቀፈ ሲሆን እነዚህም የግብይቱ ደንቦችን እና የአባልነት አደረጃጀቱን ቀጣይነት ባለው መልኩ ስለመተግበራቸው ቁጥጥር ይደረግባቸዋል። ለገበያው ተደራሽነት ሲባል አባላት በራሳቸው ኃላፊነት በባለስልጣኑ መጽደቅ ባለባቸው በተወሰኑ መስፈርቶች እና ዝግጅቶች ላይ ተመስርተው ለሌሎች የገበያ ተሳታፊዎች የግብይት መድረኩን በቀጥታ እንዲያገኙ መፍቀድ የሚችሉበትም አሰራር በረቂቅ መመሪያው ተካቷል።

- ገበያው በባለስልጣኑ ክትትል የሚደረግበት ሲሆን ለዚህም ገበያው የቁጥጥር አደረጃጀቱ አካል አድርጎ በመመሪያው ላይ በተገለጸው መሰረት መረጃዎችን እና ወቅታዊ ሪፖርቶችን እና ግምገማዎችን ለባለስልጣኑ ማቅረብ እንደሚገባ በረቂቁ ተመልክቷል።

በክፍል 2 መሠረት ፈቃድ የተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ እና የተዛማጅ ውሎች የሚያገበያይ ሆኖ ያልተማከለ በጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ላይ ለመስራት የሚፈልግ ከሆነ ተጨማሪ መስፈርቱን አሟልቶ ከባለሥልጣኑ ተጨማሪ ፈቃድ መውሰድ እንደሚጠበቅበት ይደነግጋል።

7. <u>ክፍል 3 ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ (አንቀጽ 57-69)</u>

ክፍል 3 ላልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን፣ቁጥጥር እና አሰራሩን ያስቀምጣል። ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ በአዋጁ ውስጥ በሰፊው እንደተገለጸው እውቅና ከተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች ውጪ በተዋዋይ ወገኖች ፊት ለፊት ወይም እንደ ስልክ እና የኮምፒውተር መረብ በመሳሰሉ የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም የሚገበያዩበት ገበያ ነው። በአዋጁ አንቀጽ 32(1) መሠረት ለያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የሚደራጀው እና ፈቃድ የሚሰጠው በአክሲዮን ማህበር አይነት መሆን እንዳለበት ይደነግጋል።

ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድን በሚመለከት በረቂቅ መመሪያው ውስጥ መታወቅ ያለባቸው ድንጋጌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ላይ ሰነደ ሙዓለ ንዋችን ለመግዛት፣ ለመሸጥ ወይም ዋጋ ለማስገባት ብቁ የሆኑት ብቸኞቹ ሰዎች ፍቃድ የተሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላሎች ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ አከናዋኞች ናቸው። ለመገበያየት በታቀዱት የሰነደ ሙዓለ ነዋይ ዓይነቶች እና ለእነዚያ ሰነዶች በቀረቡት የእንቨስተሮች ምድብ ላይ በመመስረት ባለስልጣኑ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተገቢውን ፈቃድ የተሰጣቸውን ወይም ሌላ የሚመለከተው የፌዴራል መንግሥት አካል ግብይት እንዲፈጽሙ እና እንዲሳተፉ ሊፈቅድ እንደሚችል በረቂቁ ተፈቅዷል።

- በረቂቅ መመሪያው አንድ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የዋጋ ተመን ሥርዓቱን የውስጠ-ደንቦች እና ሥነ-ሥርዓቶችን ጨምሮ አንድ ሰው የዋጋ ተመን ሥርዓቱን እንዴት እንደሚያቀርብ እና እንደሚሳተፍ፣ የአንድ ተሳታፊ መብቶች እና ግዴታዎች እና ሌሎችንም የያዘ በባለስልጣኑ የጸደቀ የዋጋ ተመን ሥርዓት እንዲኖረው ተደንግጓል።
- ማንኛውም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የሚሳተፍ ሰው በመዝገቡ ውስጥ ስለሚገበያየው የሰነደ መዓለ ንዋይ እና ስለሰነዱ አውጪ ተገቢው መረጃ ከሌለው በስተቀር በሰነዱ ላይ የዋጋ ተመን እንዲያቀርብ የማይፈቀድለት መሆኑን፣ ይህ መረጃ ቢያንስ የቅርብ ጊዜውን ዓመታዊ ሪፖርት፣ ወቅታዊ እና ጊዜያዊ ሪፖርቶችን እንዲሁም በባለስልጣኑ የተሞሉ ጊዜያዊ ሪፖርቶችን ማካተት እንደሚገባ ተመልክቷል።
- ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ላይ የዋጋ ተመን የሚቀርብባቸው ብቁ የሆኑት ሰነደ መዓለ ንዋዮች በኢትዮጵያ የሰነደ መዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም በሌላ ፈቃድ ባለው የሰነደ መዓለ ንዋይ ገበያ ላይ የማይገበያዩ ሰነዶች ብቻ ናቸው። ይህ ገደብ ቢኖርም በገበያው በሚዘጋጀው እና በባለስልጣኑ በሚጸድቀው ውስጠ-ደንብ መሠረት የእነዚህ ትልልቅ ሰነዶች ግብይት (large block trades) ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ውስጥ ሊሸጥ እንደሚችል በረቂቁ ተደንግጓል። ከዚህም በተጨማሪ የመንግስት ሰነደ መዓለ ንዋዮች ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ላይ ሊገበያዩ ይችላሉ።
- ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድን ለማጽደቅ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማሟላት ሲባል ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ በባለስልጣኑ ቁጥጥር የሚደረግበት መሆኑን፣ የመመሪያውን መስፈርት የሚያከብር ስለመሆኑ ለማሳየት ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ቀጣይነት ያለው ወቅታዊ ሪፖርቶችን እና ግምገማዎችን ማቅረብ እንደሚጠበቅበት በረቂቁ ተደንግጓል።

8. <u>የካፒታል መስፈርቶች</u>

መመሪያው የኢትዮጵያ ሰነደ መዓለ ንዋዮች እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ጨምሮ ሌሎች ገበያዎች ማቋቋሚያ የሚሆን "ዝቅተኛ ካፒታል" ያካትታል። ዝቅተኛው የካፒታል መጠን ስራውን ለማስጀመር የሚበቃ ሆኖ በሂደት የገበያው ስራ እና ስጋት እየታየ ሊጨመር እንደሚችል ተደንግጓል። በኢትዮጵያ ገበያ ውስጥ እንደ የሰነደ መዓለ ንዋዮች ገበያ፣ የተዛማጅ ውሎች ገበያ እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ለመመስረት የሚፈለገው ዝቅተኛ ካፒታል በተለይ የገበያ ልማት ዓላማዎችን እና በሂደቱ መጀመሪያ ላይ ለኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ የሚያስፈልገውን የገበያ እና የግብይት መድረኮች ብዛት ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

በተጨማሪም የሚፈለገው የካፒታል መጠን የገበያውን ዕድገት እንዲሁም ፈቃድ ያለው አካል የተለዩ የንግድ እቅዶችን እና የገበያ አሠራርን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ይህ አካሄድ በአለም አቀፍ የሰነደ መዓለ ንዋዮች ተቆጣጣሪዎች ማህበር (IOSCO) ከተቀመጠው በካፒታል ገበያ ስጋት ላይ የተመሰረተ የቁጥጥር አይነት ጋር የሚስማማ ነው። ይህ ድርጅት

በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ቁጥጥር ውስጥ አለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን የሚያወጣ ድርጅት ነው።

በመጨረሻም በረቂቅ መመሪያው ክፍል 4 መሠረት በሃገራችን የካፒታል ገበያ ገና ያላደገ እንደመሆኑ ለገበያ እና ላልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ ለሚጠይቁ አመልካቾች እና ፈቃድ አግኝተው በስራ ላይ የሚገኙም ቢሆኑ የማያሟሏቸው መስፈርቶች ሲኖሩ የባለሥልጣኑ ቦርድ የገበያ ልማት አላማ መሠረት በማድረግ አንዳንድ መስፍረቶችን በረቂቅ መመሪያው ከተጠቀሰው መስፈርት ሊቀንስ ወይም ሊተው እንደሚችል ተመልክቷል።